# የአቶ መለስ መንግስት ልማታዊ ወይስ አጥፊ አገዛዝ ?

## መግቢያ

በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢህአዴግ አገዛዝ ስልጣን ከጨበጠ ይኸው 21 ዐመት ሆነው። በዚህ ወደ አንድ ትውልድ የሚጠጋ የአገዛዝ ዘመን በአቶ በረከት ሰምኦን አገላለፅ „ኢህአዴግ ብዙ ውጣ ውረዶችን እንዳሳለፈና ፣ ኢኮኖሚውም በአስተማማኝ መሰረት" ላይ እንደቆመ አብስረውልናል። እንደሚሉን ከሆነና መንግስታቸውም ሊያሳምነን እንደሚሞክረው ይህ <በፀና መሰረት ላይ የቆመው ኢኮኖሚ> አገዛዛቸው መንግስት በሚከተለው „ለልማት አትኩሮ በሰጠው የኢኮኖሚ ፖሊሲ" አማካይነት ነው። በሌላ አነጋገር የሚሉን ፣ የኢህአዴግ አገዛዝ 21 ዐመት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲያደርግ የነበረውና ዛሬም የሚያካሄደው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሌላ ሳይሆን ልማታዊ የመንግስት(Developmental State) ፖሊሲን ዋናው መመሪያው በማድረግ ነው።

ኢህአዴግ ስልጣን ከጨበጠ ወዲህ በተለይም ባለፉት አስራአምስት ዐመታት ከፍተኛ የሆነ በአፍሪካ ውስጥ ተወዳዳሪነት የሌለው የኢኮኖሚ ዕድገት ታይቷል እየተባለ ሲነገረን ከርሟል። እንደ ዓለም የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የመሳሰሉት ይህንን የእነ አቶ መለስን የኢኮኖሚ ዕድገት ትክክል ለመሆኑ ያረጋግጣሉ። እዚህ ባለንበት አገርም ስለአፍሪካ የኢኮኖሚ ዕድገት ሲወራ ፈረንጆች ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት አንድ ሰሞን ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች በአማካይ ወደ ስድስት በመቶ የሚጠጋ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዳሳዩና ፣ ይህንን ዐይነቱን ዕድገት የምዕራብ አውሮፓ የካፒታሊስት አገሮች ሊደርሱበት እንደማይችሉና የሚኳትትም እንደሆነ አብስረውልናል። እንደዚህ ዐይነቱን <የመረቃ ዕድገት> ካስመዘገቡት አገሮች ውስጥ አንዷ በኢህአዴግ አገዛዝ የምትመራው ኢትዮጵያችን እንደሆነች ተነግሮናል። አሁን ደግሞ በቅርቡ ዘ ሰን ተብሎ የሚጠራው የእንግሊዝ ጋዜጣ ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ጋር ስትወዳደር የኢኮኖሚ ዕድገቷ በአስር እጥፍ እንደሚበልጥ አብስሮልናል። እነዚህን የመሳሰሉት አብዛኛውን ጊዜ ምንም ዐይነት ሳይንሳዊ መሰረትና ይዘት የሌላቸው ድጋፍና አገላለጾች በአንድ በኩል እንደነ አቶ መለስ ለመሳሰሉት አገዛዝ ቀጥተኛ ድጋፍና የስልጣን ዕውቅና ሲሰጡ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ይህንን ያህልም ስለኢኮኖሚ ዕድገትና ስለሰውልጅ ስልጣኔ ጠለቅ ብሎ ለማየት ለማይችልም ሆነ ለማወቅ ለማይፈልግ ማደናገሩ የማይቀር ነው። በዚህም ምክንያት የተነሳ አንዳንድ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ከአሜሪካም ሆነ ከአውሮፓ ወይም ሌላ ከውጭ አገር ከብዙ ዐመታት ቆይታ በኋላ ወደ አገራቸው ፣ በተለይም ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ትላልቅ ፎቆችና መንገዱን ያጣበቡ ትላልቅና አዳዲስ መኪናዎችን ሲያዩ ሲነገራቸው የከረመው ዕውነት እንደሆነ ለማመን ጥቂት ደቂቃም አይፈጅባቸውም። ውይ አገራችን! እንዴት አድጋለች ማለታቸው አይቀርም።

ወደ ኢህአዴግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ዋና ይዘትና ፍልስፍና ስንመጣ እነ አቶ መለስ እስከአሁን ድረስ ተግባራዊ ሲያደርጉት የከረሙት ፖሊሲ ልማታዊ የመንግስት ፖሊስን መሰረት ያደረገ የተሃድሶ የአገር ግንባታ ክንዋኔ እንጂ በኒዎ-ሊበራሊዝም መሰረተ-ሃሳብ ላይ የተመረኮዘ አይደለም እያሉን ነው። እንዲያውም አልፈው ተርፈው ኒዎ-ሊበራሊዝም ምን እንደሆን ለማያውቀው ህዝባችን ተቃዋሚው ኃይሎች የኒዎ-ሊበራሊዝምን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የሚታገሉ ናቸው እያሉ ማደናገር ጀምረው እንደነበርና ዛሬም እንደሚያደርጉ የታወቀ ጉዳይ ነው። ይሁንና ከአንድ ሁለቴ በስተቀር የኒዎ-ሊበራሊዚምን የኢኮኖሚ ፍልስፍና በሚመለከትና ፣ የኢህአዴግ አገዛዝም እስከዛሬ ድረስ ተግባራዊ ሲያደርግ የነበረውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንድ በአንድ ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማነፃፀር ሰፊ ትንተናና ትምህርት ከተቃዋሚው ኃይል የተሰጠ ምንም ነገር የለም። ስለሆነም „የሌባ

ዐይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ“ እንደሚሉት አነጋገር የአቶ መለስ አገዛዝ ማንም የሚጋፈጠኝ የለም ፣ የኔን ፖሊሲ ትክክለኛነት የሚያረጋግጡልኝ ዓለም አቀፋዊ ኢንስቲቱሽኖች ፣ እንደ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የመሳሰሉት አሉ በማለት አሁንም የማያስፈልግ ውዥንብር እየነዛ ነው። ሰሞኑን ደግሞ <የፌዴራሉ መንግስት> ስለ ድህነት ጉዳይ እንዲጠና በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ፣ በተለይም በአዲስ አበባ ውስጥ ያለው ድህነት ካለፈው አምስት ዐመታት ጋር ሲወዳደር ከ38.7 በመቶ ወደ 29.6 በመቶ ቀንሷል በማለት መዝናናት ጀምሯል። ይሁንና ሌሎች ጥናቶች እንደሚያረጋግጡትና የተጨባጩም ሁኔታ እንደሚያሳየን ፣ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሀብታምና በደሀ መሀከል ከፍተኛ የገቢ ልዩነት እንዳለ ነው። በተጨማሪም ከቆሻሻ እየለቀመ የሚበላ ከሰማንያ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ የሚጠጋ ህዝብ በአዲስ አበባ ብቻ እንደሚገኝ የታወቀ ጉዳይ ነው። አሁን በቅርብ በዓለም ባንክ የወጣው የሚሌኒዩም 2015 የኢኮኖሚ ግቦች <በአብዛኛው አገሮች ተግባራዊ መሆን> የሚያበስረው ሪፖርት እንደ አቶ መለስ የመሳሰሉትን አገዛዝ ሊያዝናናቸውም ቢችልም በግልጽ የሚታየውን ነገር ማንም ሊክደው አይችልም። በተጨማሪም የነ ፕሮፌሰር ስቲግሊትዝ ግልጽ ድጋፍና በቅርብ ታትሞ በወጣው መጽሀፋቸው ውስጥ ,,Good Growth and Governance in Africa ,, በሚለው እነ አቶ መለስ ያቀረቡት አስተዋጽዖ“States and Markets: Neoliberal Limitations and the Case for a Developmental State“ በአንድ በኩል ብዙዎቻችንን ሊያሳስትና ሊያዘናጋ ሲችል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ከእነ ፕሮፌሰር ስቲግሊትዝ የሚሰጠውን ግልጽ ድጋፍ በይፋ ለመዋጋት ያስቸግራል። የሚያስቸግረው ድጋፋቸውን ፋርሽ ለማድረግ ሳይሆን የኖቬል ዋጋ ተሸላሚ ስለሆኑ የሳቸውን ለአቶ መለስ የሚሰጡትን ድጋፍ ውድቅ ለማድረግ ቢቻልም እንኳ በቀላሉ አመኔታ  ለማግኘት ሰለማይቻልና <አንተ ደግሞ ማን ሆነህ ነው እኚህን የመሰሉ ታላቅ የኢኮኖሚ ሊቅ የምትጋፈጣቸው> የሚሉ አጉል ዘመቻ ስለሚያካሄዱ ነው። በተለይም በኢኮኖሚ ቲዎሪ የፍልስፍና ትግል ውስጥ የተለያዩ አመለካከቶች እንዳሉ ለማያውቁና ፣ ከፍተኛ ትግልም ተካሂዶ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ እንደተገነባ ለማይገነዘቡት እነ ፕሮፌሰር ስቲግሊትዝ ለአቶ መለስ የሚሰጡት ድጋፍ ሊያሳስታቸው እንደሚችል በቀላሉ መረዳት ይችላል። እዚህ ላይ እንዲታወቅልኝ የምፈልገው ፕሮፌሰር ስቲግሊትዝ ለእነ አቶ መለስ ቀጥተኛም ሆነ ተዛዛዋሪ ድጋፍ ቢሰጡም በአሁኑ ወቅት አሉ ከሚባሉ የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚስቶች አንዱ ሲሆኑ ፣ በተለይም በሶሻል ፎረም ላይ እየተገኙ ስለሶስተኛው ዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታና ስለ ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ መዛባት የሚሰጡት ትንተናና ድጋፍ የሚያስመሰግናቸው ነው። ይሁንና ግን የሚሰጡት ትንተና የተወሰነን ሎጂክ በመከተል ሲሆን ፣ ከሳቸው አቀራረብ ጋር የማይስማሙም እንዳሉ ግልጽ መሆን አለበት።በተለይም በየአገሮች ውስጥ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ከውጭው ጋር ስላለው መቆላለፍና ይህም በራሱ ለዕድገት እንቅፋት መሆኑን በቲዎሪያቸው ውስጥ ለማጠቃለል እይጥሩም ወይም አይፈልጉም። ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ከፖለቲካዊ ሁኔታ አስቾጋሪነትና አመችነት እንዲሁም ከጥገና ለውጥ አስፈላጊነት ጋር ለማያያዝ አይቃጡም። ያም ሆኖ የተወሰነ ሃሳባቸውን ብንጋራምና ለሶስተኛው ዓለም ያላቸውን ወገናዊነት ብንቀበልም ለምን ግን ከእንደዚህ ዐይነቱ ግራ ከሚያጋባ አመፀኛ መንግስት ጋር ቆመው ግራ እንደሚያጋቡን ግልጽ አይደለም።

ወደ ልማታዊ መንግስትና በፀና መሰረት ላይ ስለቆመው ኢኮኖሚያችን ስንመጣ አቶ መለስም ሆነ አቶ በረከት ሰምዖን ፅንሰ-ሃሳቦችን ከመሰንዘራቸው በስተቀር ፍልስፍናቸው ምን እንደሆነና ፣ በፀና መሰረት ላይ የቆመው ኢኮኖሚያቸው ምን እንደሚመስል በግልጽ አላስረዱንም። ስለዚህም ይህንን በሰፊው የመተንተኑና አንባቢውን የማስረዳቱ ጉዳይ እኛ ለተከበረችና ፣ በሳይንስና በቴኮኖሎጂ እንዲሁም ባሸበርቁ ከተማዎች ማበብ ስላለባት ኢትዮጵያ ለምንታገለው ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ትከሻ ላይ የወደቀ ነው ማለት ነው። ስለዚህም እነዚህን ሽንጣቸውን ገትረው ዐይን ያወጣ ውሸት የሚነዙትን የኢህአዴግ ባለስልጣናት ማጋለጥ ያስፈልጋል።

# ግልጽ መሆን ያለባቸው ፅንሰ-ሃሳቦች- የልማታዊ መንግስትና የተሃድሶ ትርጉም!

በመጀመሪያ ደረጃ የልማት ተቃራኒው ጥፋት ነው። ማውደም ማልት ነው። ስነ ስርዓት ያላቸውን ነገሮች ማዘበራረቅ ወይም እንዳልነበሩ ማድረግ ጥፋት ይባላል። ሳይንሳዊ መሰረት የሌላቸውንና ዕውነተኛ ሀብት ለመፍጠር የማያስቾሉና ፣ እንዲሁም የመንፈስ ተሃድሶ የማያመጡ የኒዎ-ክላሲካል ወይም የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንደጥፋት ይቆጠራል ፤ ወይም እንደምናየው ውጤታቸው ጥፋት ነው። ጥፋት በተለያዩ መልኮች ሊገለጽ የሚችልና አብዛኛውን ጊዜም ከአእምሮ መበላሸት ጋር ሊያያዝ የሚችል አጉል ድርጊት ሲሆን ፣ በሌላ ወገንም ከባህል ተሃድሶ ጉድለት ወይንም ጭንቅላትን በጥሩ ዕውቀት ካለመግራት የተነሳ አንዳንድ አመፀኛ ሰዎች በሌላው ላይ ወይም በአካባቢ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት እንደጥፋት ይቆጠራል። በተጨማሪም ብዙም ሳያወጡ ሳያወርዱ ዛፎችን እንዳለ ማውደም ፣ ስለአአካባቢ ሁኔታ በቂ ጥናትና ግንዛቤ ሳይኖር የጥሬ-ሀብት ለማውጣት ሲባል መሬትን መቦደስና መሬት ውስጥ ያለውም ውሃ እንዲመረዝ ማድረግ እንደጥፋት የሚቆጠር ነው። አንድ ግለሰብም ሆነ በአንድ አካባቢ የሚኖር ህዝብ አርቆ ከማሰብ ጉድለት የተነሳ በተፈጥሮ ላይ የሚያደርሰው መዘበራረቅ ወይም የአካባቢ መዛባት እንደጥፋት ሊቆጠር ይችላል። ተፈጥሮም ሲያገረሽባት የመሬት መንቀጥቀጥ የመሳሰሉትን ውርዥብኝ በመላክ አንድን ከተማ ድምጥማቱን ታጠፋለች። ለምሳሌ የዛሬ አንድ ዐመት በጃፓን የደረሰው የመሬት መንቀጥቀጥና ሱናሚ ተፈጥሮ ሲያገረሽባት የምታደርገው ነገር ነው ልንለው እንችላለን። በሌላ በኩልም <ጤናማ ጥፋት> ይኖራል። ይህም ማለት ለምሳሌ አንድ ህዝብ ከተዝረከረከ ኑሮ ስነ ስርዓት ያለው ኑሮ ለመመስረት ሲፈልግ ከተማዎችን ይቆረቁራል። በዚህን ጊዜ የግዴታ ደንን በመመንጠር እንደ ማሰብ ኃይሉ ውበት ያለው ከተማ ወይንም በስርዓት ያልታቀደ ከተማ ይሰራል። ይሁንና ግን ዛፎችን በመቁረጥና መሬትን በመቆፈር የተፈጥሮን ህግ ያናጋውን ያህል ፣ በተፈጥሮ ውስጥ በሚከሰቱ አደጋዎች እንዳይረበሽና አካባቢውም እንዳይናጋ ከፈለገ ከተማን ለመገንባት የሚወስዳቸው ዕርምጃዎች በሳይንስ የተጠኑ መሆን አለባቸው።

ከዚህ ስንነሳ ዕድገት (Development) በቅራኔዎች የተዋጠ ነው ማለት ነው። የሰው ልጅ የማሰብ ኃይል ስላለውና በቁጥርም እየጨመረ ስለሚሄድ የግዴታ አካባቢውን ማልማት አለበት። አካባቢውን ለማልማት ደግሞ በማሰብ ኃይሉ በየጊዜው የተሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች(Instruments of Labour) መፍጠርና መስራት አለበት። በዚህ መሰረት በአንድ በኩል ስራውን ሲያቃልል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ምርታማነትን ይጨምራል። በተጨማሪም በተፈጥሮ ላይ የተወሰነ የመቆጣጠር ኃይልን ያገኛል። ዕድገት(Development) እንደ ሰዎች ወይም አገዛዞች ንቃተ ህሊና የተለያዩ መልኮች የሚኖሩትና አቅጣቻዎችን የሚይዝ ነው። እንደየምሁራን ዕውቀት አቀሳሰምና የርዕዮተ-ዓለም ዝንባሌ ዕድገት የተለያየ ትርጉም ይሰጠዋል። በአውሮፓ ምድር ውስጥ በመርካንትሊዝም አማካይነት እንደ እንግሊዝ ያሉ አገሮች ኢኮኖሚያቸውን ከገነቡና ካጠናከሩ በኋላ ሌላው አገር የነሱን ፈለግ እንዳይከተል ሲሉ በመርካንትሊዝም ላይ ዘመቻ በመክፈት የነፃ ንግድን አርማ ማውለብለና መስበክ ጀመሩ። ስለሆነም ከአስራስምንተኛው ክፍለ-ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ዕድገት የሚለው ፅንሰ-ሃሳብ የግዴታ በርዕዮተ-ዓለም ሽፋን በመሸፈን የበለጠ አወዛጋቢና ውዥንብር ነዢ የሆነ የመጣ ፅንሰ-ሃሳብ ለመሆኑ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። በተለይም ካፒታሊዝም የበላይነትን ከተቀዳጀ ከአስራዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን አንስቶ ፣ ይበልጥ ደግሞ በሃያኛው ክፍለ-ዘመን ለሶስተኛው ዓለም አገሮች ተብሎ የወጣው የኢኮኖሚ ዕድገት ትምህርት የዕድገት ፅንሰ-ሃስብ እንዲጣመም በማድረግ የሰው ልጅ እንዲሰቃይና ተፈጥሮም እንዲበዘበዝ አድርጓል ፤ እያደረገም ነው።

ይሁንና ግን የዕድገትን መሰረተ-ሃሳብ ወደ ኋላ ተመልሰን በጥሞና ስንመረምረው እንደዛሬው ዐይነት በጥፋት ላይ ያተኮረና የሰውን ልጅ ወደ ባርነት የሚገፈትር ፣ ወይም አንዱን የበላይ ሌላውን ደግሞ ተገዢ የሚያደርግ ፅንሰ-ሃሳብ አይደለም። ዕድገት ሲባል የተስተካከለና የተሟላ ነው። በተለይም በነሶክራተስ የተደረሰው ፍልስፍና እንደሚያስተምረን በአጠቃላይ በተፈጥሮ ውስጥ ተፈጥሮን የሚገዛት የኮስሞስ ኃይል(Cosmic Order) አለ።በዚህ ህግ መሰረት ተፈጥሮ ራሷን በማጥፋትና በማደስ ፣ እንዲሁም አዳዲስ ዕፅዋትንና ኃይሎችን በመፍጠር በዘለዓለማዊ ተንቀሳቃሽኒነት የምትገኝ ነች። ስለዚህም ይላል ላይብኒዝ እግዚአብሄር ከፕላኔቶች ሁሉ ለሰው ልጅ ተስማሚው የሆነቸውን ሁሉን ነገር የምታሟላውን ፍጥረ-ነገሮች ያየዘች መሬትን ፈጥሮልናል። በመሆኑም የሰው ልጅ የኮስሞስንና የተፈጥሮን ህግ በመረዳት ለሱ የሚሆነውን የዕድገት ፈለግ መቀየስ አለበት። በመሆኑም ዕድገት ሲባል በአንድ ቦታ ላይ የሚካሄድ ፣ እዚያ ቦታ ብቻ የሚቀርና ተፈጥሮንና የሰውን ልጅ ኑሮ የሚያናጋ አይደለም። ዕድገት ሲባል በይዘቱ ሁለንታዊ ሲሆን ከታች ወደ ላይ ቀሰ በቀስ በሁሉም አቅጣጫ ውበት ባለው መልክ እያደገና እየሰፋ የሚሄድ ነው። በተጨማሪም ዕድገት ሲባል አንድ ወጥ አይደለም። በተፈጥሮ ውስጥ አንድ ዐይነት ዛፍ ወይም አንድ ዐይነት አበባ እንደሌለ ሁሉ ፣- ምክንያቱም ተፈጥሮ ሚዛናዊነት የሚኖራት የተለያዩ ነገሮች ተቻችለው ሲኖሩና አንድ ወጥ ነገር ተፈጥሮን ስለሚቀናቀን ነው- በህብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥም  ዕድገት ሲባል ሁሉንም ነገሮች ያካተተ ነው። ይህም ማለት ፓለቲካዊ ወይም ኢንስቲቱሽናዊ ፣ ባህላዊና ህብረተሰብአዊ ወይም ማህበራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ልወጦችን ያካተተ ነው። እነዚህ አንድ ላይ ተጣምረው የሚሂዱ ናቸው። አንደኛው ከሌላው  ተነጥሎ ሊታይ የሚችል አይደለም። ልክ አንድ ህጻን ልጅ የተሟላ አሰተሳሰብና ዕድገት እንዲኖረው ከተፈለገ ከተወለደ ጀምሮ ለአቅመ-አዳም እስኪደርስ ድረስ ከፈተኛ እንክብካቤ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ፣ ህብረተሰብአዊ ዕድገትም እንደዚሁ ከተቻ ወደላይ በጥንቃቄና በከፍተኛ ዕውቀትና ዕውቅና የሚካሄድ ነው። ዕውነተኛ ዕድገት ከላይ ወደታች የሚጫን አይደለም ፤ ወይም የጥቂት ሰዎችን ፈላጎት ለማሟላትና እነሱ በአቀዱት ዕቅድ የሚካሄድ አይደለም። ዕውነተኛ ዕድገት ከፍተኛ ዕውቀት ባላቸው ስዎች ቢነደፍም ፣ የመጨረሻ መጨረሻ ግን በአንድ አገር ውስጥ  የሚኖርን ህዝብ የሚያሳትፍና የዕድገትንም ትርጉም እንዲረዳው የሚያደርግ መመሪያ ነው። ለምን እንደሚኖር ፣ ምንስ መሰራት እንዳለበትና ወዴትስ ማምራት እንዳለበት እንዲገነዘበው የሚያደርግ ነው።

ስለዚህም ነው ከግሪክ ስልጣኔ ጀምሮ በኋላም እስከዛሬይቷ ቱርክ ድረሰ የተስፋፋውን የዕድገት ፈለግ ስንመለከትና ፣ በተለይም ከአስራሶስተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ የተካሄደውን የመጀመሪያውን የሬናሳንስ(Early Renaissans Period) እንቅስቃሴና የከተማ ግንባታ ፣ እንዲሁም በነዳንቴ የተደረሰውን የአምላኮች ኮሜዲስ ስናነብ የምንረዳው ዕውነተኛ ዕድገት ሊመጣ የሚችለው የሰው ልጅ ከጨለማና ከጥፋት አስትሳሰቡ የተላቀቀና ቀናውን መንገድ የተከተለ እንደሆን ብቻ ነው። ስለዚህም በፕሮፌሰር ኤሪክ ዕምነት ዕውነተኛ ዕድገት የሰውን አዕምሮ በቁጥር ውስጥ የሚያስገባ መሆን አለበት። ምክንያቱም ጥፋትም ሆነ ዕድገት የሚባለው ነገር ባለማሰብም ሆነ በማሰብ ኃይል እየተረዱ ተግባራዊ የሚሆን በመሆኑ የግዴታ በመጀመሪያ ደረጃ የመንፈስ ተሃድሶ ያስፈልጋል ማለት ነው።

ከዚህ ስንነሳ ኢትዮጵያ ውስጥ በእነ እቶ መለስ የሚለፈፈው የተሃድሶ ሂደት በጭንቅላቱ የቁመ ነው። ተሃድሶ ማለት ሌላ ሳይሆን ሬናሳንስ ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ ዕውቀትን መልሶ ማግኘት ማለት ነው። ፅንስ-ሃሳቡም የግዴታ ከግሪክ ፍልስፍናና ሳይንስ እንዲሁም በልዩ ልዩ ነገሮች የሚገለጸው ስልጣኔ ፣ ማለትም በድራማ ፣ በፖለቲካል ዲስኮርስ ፣ በአርክቴክቸር ፣ በስክለፕተርና በተለያዩ ጥንታዊ ስዕሎች ... ወዘተ የሚገለጸውን መሰረተ ያደረገ ነው። ዋናው መሰረተ-ሃሳቡና ዐላማውም የሰውን ልጅ ከእግዚአብሄር ጋር በማቀራረብና የመንፈስን የበላይነት እንዲቀዳጅ በማድረግና ፣ በተጨማሪም ሙሉ በሙሉ ግለሰብአዊ ነፃነት እንዲቀዳጅ በማድረግ የሚኖርባትን ምድር እንደ ኮስሞክ ስርዓት ውበት እንዲኖራት እንዲያደረግ ነው። ከአስራሶስተኛው ክፍለዘመን ጀምሮ የግሪክ ሊትሬቸር ወደ ላቲን ሲተረጎም ርብርቦሽ የተተደረገበት የግሪኩን ስልጣኔ ዋና

ሃሳብ ለመረዳት ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አነዳንቴ በቀደዱት ፈለግ አንድ ትውልድ በአዲስ ሃሰብ በመታናጽ ለስልጣኔ ይነሳል። ራፋኤል ፣ ዳቤንቺ ፣ ሚካኤል አንጀሎ ፣ ፔትራርካና ሌሎችም በሺህ የሚቆጠሩ በአንድ ጊዜ ከሰማይ እግዚአብሄር እንደወረወራቸው ለስልጣኔ ታጥቆ በመነሳት ተዓምር ይሰራሉ። ጣሊያንን በአንድ ጊዜ ይለውጧታል። ይህ ዐይነቱ በጣሊያን የተከሰተው የተሃድሶ እንቅስቃሴ ወደ ሌሎች የምዕራብ አውሮፓ አገሮችም በመተላለፍ ምሁሩን ያዳርሳል። ሁሉም በዚህ በተቀደሰ ዕውነተኛ የዕድገት ፈለግ ይሳከራል። ተፈጥሮን በመቃኘት ውብ ውብ ነገሮችን ይሰራል። ከዚህ ስንነሳ ተሃድሶ ማለት ሁለንታዊና ከጭንቅላት በመነሳት ወደታቸ በመውረድ ተፈጥሮን በአዲስ መልክ የሚቀርጽ ነው። ተሃድሶ ማለት ተፈጥሮን እንዲያው ተብዝባዥ የሚያደርጋት ወይንም ነፍስ እንደሌላት የሚቆጥር እንቅስቃሴ አይደለም። ተፈጥሮም እንደሰው ልጅና እንሳሳት ውስጣዊ ህይወት ያላትና ፣ በውስጣዊ የመንቀሳቀስ ኃይሏም ለህይወታችን የሚሆኑ ነገሮችንም የምትለግሰን ስለሆነ በዕድገት ስም የሚወሰዱ ዕርምጃዎች በሙሉ የተፈጥሮን ህግ የሚጥሱ መሆን የለባቸውም።

ችግሩ ካፖታሊዝም የበላይነትን ሲቀዳጅ ይህንን የተሃድሶንና የዕድገትን ትርጉም በአፍጢሙ በመድፋት ተፈጥሮንና ሰውን ተብዝባዥ ያደርጋቸዋል። ሁሉም ነገር ለትርፍ የሚሰራና ፣ ማንኛውም ነገር ከዋጋና ከጥቅም(Cost-Benefit)አንፃር የሚተመን ይሆናል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዕድገት ሲባል ከተወሰነ የህብረተሰብ ግኑኝነት ጋር የተያያዘ ነው። የግዴታ የኢኮኖሚና የፖለቲካን የበላይነትን የተቀዳጀውን የህብረተሰብ ክፍል ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ነው። የማንኛውም ሰው አስተሳሰብ በዚህ በየጊዜው እየዳበረ ግን ደግሞ የሰውን ልጅ የማሰብ ኃይል እያቀጨጨው ከሚሄድ የተንዛዛ የፍጆታ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ ነው። የሳይንስና ቴክኖሎጂም ዕድገት ከዚህ የካፒታሊዝም ዕድገት ሎጂክ ጋር የተያያዙ እንጂ በምንም ዐይነት የሰውን ልጅ ስራም ሆነ ኑሮ ለማቃለል እየተባሉ የተፈጠሩ አይደሉም። ካፒታሊስቶች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ማድረግ የሚፈልጉት ከፍተኛና ተከታታይ ትርፍ ያመጣልናል ብለው የገመቱ እንደሆን ብቻ ነው። ለምሳሌ ኃይልን በማመንጨት ከሰድሳና ከሰባ ዐመታት በፊት ለማንኛውም ቤተሰብ የሚዳረስ ከፀሀይ የሚፈልቅ ኃይል ዳብሯል። ይህ ግኝት ግን እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የተቀበረ ነበር። በየጊዜው በሚደርሰው የኒውክላር ኃይል አደጋና ፣ በተለይም ደግሞ የራዲዮአክቲቭ ቆሻሻዎችን መጣያ ቦታ አስቸጋሪ ስለሆነና ከህዝብም ከፍተኛ ግፊት በመፈጠሩ ካፒታሊስቶች ስትራቴጂያቸውን እንዲቀይሩ ተገደዋል። እንደዚሁም አሁን ለመኪና ቤንዚንና ዲዝልን ከመጠቀም ይልቅ ወደ ኤልክትሮ ባትሪዎች ለመሸጋገር በማምራት ላይ ናቸው። ባጭሩ ከአራስምንተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ ከገዢዎች አስተሳሰብ ውጭና የነሱን ጥቅም ከሚያንፀባርቅ የዕድገት ፈለግ ሌላ ዕድገት የለም። በሃምሳኛው ዐመትም ሆነ ዛሬ ስለዕድገት ሲወራ ከካፒታሊዝምና ከግሎባል የካፒታሊዝም እንቅስቃሴ ሎጂክ ጋር የተያያዘ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ወደሶስተኛው ዓለም አገሮች ስንመጣ ፣ በተለይም አሜሪካን የበላይነትን ከተቀዳጀ ወዲህ በአሜሪካን ምህሮች ለሶስተኛው ዓለም አገሮች ተብሎ የተዘጋጀ ዘመናዊነት(Modernization) የሚባል የዕድገት ፈለግ አለ። በዚህ ዙሪያ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰፋ ያለ ክርክር ተካሂዷል። ኒዎ-ማርክሲስት በሚባሉና በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፒታሊዝም አማካይነት የተካሄደውን የተዛባ ዕድገትና ያልተስተካከለ የንግድ ግኑኝነት እንቅስቃሴ በመቃውም ሰፋ ያለና አመርቂ ጥናት አካሂደዋል። እንደዚሁም በመልቲ ናሽናል ኩባንያዎች የሚካሄደውን የተቀጠበ በሶስተኛው ዓለም አገሮች ርካሽ የሰውን ጉልብት ለመጠቀምም ሆነ ለመበዝበዝ ሲባል የሚተከሉትን ኢንዱስትሪዎች አስታኮ ሰፋ ያለ ጥናትና ክርክር ተካሂዷል። በሌላ አነጋገር ፣ በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ ፍጹም የበላይነትን የተቀዳጀው ጎሎባል ካፒታሊዝም በየአገሮች ውስጥ እየገባ አላዋቂ መሪዎችንና ምሁራንን ተገን በማድረግ ተግባራዊ ያደረገው መጠነኛ የኢንዱስትሪ ተከላዎች በየአገሮች ውስጥ ከፍተኛ መዛባትንና የሀብት መባከንን አስከትሏል። በሃምሳኛው ክፍለ-ዘመን የምትክ-ኢንዱስትሪ(Import-Substitution-Industrialization) እየተባለ በአፍሪካና

በማዕከለኛውና በላቲና አሜሪካ አገሮች የተካሄደው ዕድገት የሚመስል የኢኮኖሚ ፖሊሲ በዓለም አቀፍ ደረጃ ልዩ ዐይነት የፍጆታ አጠቃቀምን አስፋፍቷል። በዚያው መጠንም በአንድ በኩል የመንግስታትን የመጨቆኛ መሳሪያዎች ሲያጠናክር ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ሀብት በጥቂት ሰዎች እጅ እንዲከማች በማድረግ ወደ ውስጥ ከፊተኛ የሆነ የዕድገት መዛባት እንዲፈጠር አድርጓል። የከተማዎች ካለዕቅድ መሰራትና ፣ ስራ ለመፈለግ ሲል ወደ ከተማዎች በመፈለስ ጥቂት ከተማዎችን ማጣበብ የጀመረውና በአልባሌ ስራዎች የተሰማራው የዚህ ዐይነቱ የተሳሳተ የግሎባል ካፒታሊዝም የዕድገት ሎጂክ እንቅስቃሴ ውጤት ነው። ይህ ዐይነቱ የዕድገት ፈለግ ውጤት አላማጣም ከተባለ ወዲህ በአፍሪካ ምድር ውስጥ መሰረታዊ ፍላጎትን(Basic Needs) ከማሟላት ከሚለው መመሪያ ጀምሮ በአረንጓዴው አብዮት (Green Revolution) ውስጥ በማለፍና እስከመዋቅር ማስተካከያ(Structural Adjustment Program)ድረስ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የዕድገት ፈለግ እንደየጊዜው ለግሎባል ካፒታሊዝም በሚስማማ መልክ በመቀየስ ምን ማድረግና እንዴትስ መራመድ እንዳለባቸው ተወስኗል። ይህም ማለት እያንዳንዱ የሶስተኛው ዓለም አገር በራሱ አነሳሽነትና ለራሱ ፍላጎት የሚሆነውን የዕድገት ፈለግ እንዳይቀይስ ከመጀመሪያውኑ በመታገድ መንገዱ ሁሉ እንዲጨልምበት ሆኗል። በተለይም በዘጠናኛው ዓመት የተስፋፋው ግሎባላይዜሽን የሚባለው አዳዲስ ተዋንያንን በመፍጠር ኢንቬስተሮች የሚባሉት እንደ አሸን በመፍለቅ የአፍሪካን የጥሬ ሀብት ወደ መቆጣጠር አመርተዋል። ሆቴል ቤቶችና ትላልቅ አፓርትሜንቶችን መስራቱ ከዚህ ዐይነቱ የግሎባል ካፒታሊዝም እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ሲሆን ፣ እንደገና አዲስ የፍጆታ አጠቃቀም በማስፋፋት ሀብት በከፍተኛ ደረጃ እንዲባክንና ሰፊው ህዝብም በኑሮ ውድነት እንዲሰቃይ የተደረገብትን ሁኔታ እንመለከታለን። አገራችንም የዚህ ዐይነቱ ሰለባና ህዝቦቿም በከፊተኛ ደረጃ የሚፈናቀሉባት አገርና በአዲሱ የገዢ መደብ ሰውነቷን ገልጣ እንድትሰጥ የተገደደች አገር ሆናለች። የእነ አቶ መለስ ዜናዊ የልማታዊ መንግስት እሴት ይህንን የግሎባል ካፒታሊዝምን ዘረፋ የሚያዘገጅና ህዝቦችን የሚያፈናቅል ነው።

## የልማታዊ መንግስት ምንነትና ተግባር በታሪክ ውስጥ!

አብዛኛውን ጊዜ ስለልማታዊ መንግስት ወይም ስለ ዴቬሎፐሜንታል መንግስት የሚጽፉ የኢኮኖሚስት ምሁራን የሚሰሩት ትልቅ ስህተት አለ። ይኸውም የመንግስትን በዕድገት ውስጥ ተሳትፎም ሆነ ዋና አቀናጅ መሆን ከጃፓንና ከደቡብ ኮሪያ እንዲሁም ከታይዋንና ከአንዳንድ የሩቅ ምስራቅ አገሮች ጋር ብቻ ስለሚያያዙ ነው። ይህ ዐይነቱ አቀራረብ ስህተት እንደሆነና የታሪክንም ማህደር ላገላበጠ ፣ በፕሮፌሰር ኤሪክ ራይነርት How Rich Countries Got Rich የሚለውንና ፣ በፕሮፌሰር ሊያህ ግሪንፊልድ The Spirit of Capitalism የሚለውን መጽሀፍ ላነበበና በኢኮኖሚ ዕድገት ትምህርት ውስጥ ያልተካተቱን ብዙ መጽሀፎችን ላገለበጥ የመንግስት ጣልቃ ገብነት በአጠቃላይ ሲታይ የብዙ መቶ ዐመታት ወይም በሺህ ዐመታት የሚቆጠር ታሪክ እንዳለው ወዲያውኑ ሊገነዘብ ይችላል።

ከአምስት ሺህ ዐመታት ወይም ከዚያን ጊዜ በፊት ትላልቅ ፕሮጀክቶች ፣ እንደ ቤተመንግስቶች ፣ ፒራሚዶች ፣ የመስኖ ግንባታዎችና የከተማ ቁርቆራዎች ይካሄዱ የነበረው በዚያን ዘመናት በነበሩ አገዛዞች ነበር። የግብጽ ስልጣኔ በቀሳውስቱና በፋራኦኖች የሚመራና ተግባራዊ የሚሆን ነበር። ካርል ቪትፎገል የሚባለው ታላቅ ምሁር እንደሚያስተምረን በቻይና ትላልቅ ፕሮጀክቶች ይሰሩ የነበረው ፣ በእሲያን ዲስፖቶች(Asiatic Despotism)ወይም The Hydrolic Society እያለ በሚጠራው አስተዳደር ነበር። ከክርስቶስ ልደት በፊት በአምስተኛው ክፍለ-ዘመን ተግባራዊ መሆን የጀመረው የግሪኩ ስልጣኔ ሶሎን በሚባለው ከኦሊጋርኪው መደብ በፈልቀ ታላቅ ፈላስፋና የድራማ ሰውና ታላቅ መሪ ነበር። በዘመነ ሪናሳንስ የተጀመረውንና ፣ ከፍተኛ የተሃድሶና የዕድገት ክንውን ስንመለከት የመንግስት ሚና ከፍተኛ ቦታን እንደያዘ እንገነዘባለን። በ1338 ዓ.ም የነበረው ታላቁ የሪናሳንስ ምሁር

አምብሮጊዮ ሎሬንዘቲ The Allegory of Good and Bad Government በሚለው ስራው የሚያረጋግጠው በህብረተሰብ ግንባታ ውስጥ የመንግስትን ማዕከላዊ ቦታ በማስመር ነው። ስለዚህም ይላል አምብሮጊዮ ፣ አንድ ጥሩ መንግስት በቆንጆ ከተማዎች ግንባታ ፣ በንግድ ዕድገትና እንቅስቃሴ የሚገለጽና ፣ እንዲሁም በማኑፋክቱር አብዮት ሲረጋገጥ ፣ መጥፎ መንግስት ደግሞ ህብርተሰቡን በማበላሸትና አቅጣጫውን በማዛነፍ ይገለጻል ይላል። ሰለዚህም ይላሉ ፕሮፌሰር ራይንከርት“ The usfullness of a State in the process arises out of the Renasissance concept of common weal-or the „common good“- a systemic dimension which is lost in the atomistic and static structure of today`s mainstream economics.“ በመቀጠልም በሬንሳንስ ዘመን የመንግስት ጣልቃ-ገብነት ሰፋ ያለና በዕውቅና እንዲሁም በአይዲያሊዝም ላይ በመመራት የተካሄደ መሆኑን ያረጋግጣሉ። ፕሮፌሰር አልበርት ሂርሽማን የተባሉትና ብዙ ስለ ዕድገት ኢኮኖሚክስ የጻፉ አሜሪካዊ ምሁር እንደዚህ ዐይነቱ የተቀደሰ የመንግስት ሚና ከ18ኛው ክፍለ-ዘመን ጀመሮ እየተስፋፋ የመጣው የገበያ ኢኮኖሚ በሚባለው በመተካት ነገሮች ሁሉ እየተበላሹ እንደመጡ ያመለክታሉ። በእነ አዳም ስሚዝና በኋላ ደግሞ በሄኔሪ ቱሮ የሚመራው ክንፍ የመንግስት ጣልቃ-ገብነትን በመቃወም የመንግስት ሚና እጅግ ዝቅ ማለት እንዳለበት ያስረዳሉ። ይሁንና ግን በተጨባጭ እንደታየው በተለይም ከ16ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ በምዕራብ አውሮፓ ብሄረ-መንግስታት ሲቋቋሙና ወደህብረተሰብ ግንባታ ሲያመሩ የመንግስት ሚና ከፍተኛ ቦታን እየያዘ እንደመጣ እንገነዘባለን። በታሪክ ውስጥም በግለሰብ አነሳሽነት አንድ አገር የተገነባበት ቦታና ማረጋገጫም የለም።

በዘመነ መርካንትሊዝም ከኮልበርትም በፊት የነበሩ ባለስልጣናትና ኮልበርት ራሱ ፣ በጊዜው የፈረንሳይ የገንዘብ ምኒስተር የነበረው ይመሩበት የነበረው ፖሊሲ የመንስግትን ሚና ማዕከለኛ ቦታ በመገንዘብ ነበር። ኮልበርት እንደሚለው የገንዘቡን ምንጭ ከያዝኩ ትላልቅ ስራዎችን መስራትና ህብረተሰቡን ማደራጀትን አውቅበታለሁ ይላል። ስለዚህም የፈረንሳዩ የእነኮልበርት የኢኮኖሚ ፖሊሲና በጀርመንና በአውስትሪያ ይካሄድ የነበረው ካሜራሊዝም የሚባለው የህብረተሰብ ግንባታ መመሪያ ዋናም መሰረተ-ሃሳብ አዳዲስ ዕውቀቶችን በማዳበር ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ የሚሆነውን ፈለግ መቅደድ ነበር። ስለዚህም በጊዜው የነበረው ዕምነት በቁጥር የሚለካ አንዳች የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ሳይሆን በተወሰነ አይዲያሊዝም ላይ በመመስረት ዘላቂነት ያለው ዐይነተኛና መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ነው። የሰውን ልጅ የተፈጥሮን ጸጋ በማላባስ አልፎ አልፎ ተፈጥሮ የምታደርስበትን አደጋ ለመከላከል የሚያስችለውን መሳሪያዎች በመስራት እሴት ያለው የተረጋጋ ማህበረሰብ ለመገንባት ነው። ፕሮፌሰር ራይከርት እንደገና በተፈጥሮ ሳይንስና በህብረተሰብ ሳይንስ መሀከል ያለውን ልዩነት ሲገልጹ ፣ የተፈጥሮ ሳይንስ ስለቁጥር የሚያወራ ሲሆን ፣ የህብረተሰብ ሳይንስ ግን ስለሰው ልጅና ስለኑሮው ሁኔታ መሻሻል ነው ይሉናል።“In the activist-idealistic tradition, economics and social sciences require a different kind of understanding from the natural sciences. The social sciences, concerned with ends and values instead of laws, should aim to understand (verstehen). ስለዚህም ይህ ዐይነቱን የሰውን ልጅ ምንነተና የስልጣኔ ፍላጎት ማዕከላዊ ቦታ የሚሰጥ በሃይፖቴሲስ መልክ ደጋግሞ በመጠየቅና መልስ በመፈለግ በሚገኝ ዕውቀት ብቻ ነው ተግባራዊ የሚሆነው። ይህንንም የዕውቀት ምንጭ ፒየርስ የተባለው ፈላስፋና ሳይንቲስት ተጨባጭ ሁኔታዎችን በመመልከትና በማንበብ ከዚያም በመነሳት አዲስ ቲዎሪ በመፈለግ የሚገኝ ለችግር መፍቻ የሚሆን ፖሊሲ ነው ብሎ ይጠራዋል። ከዚህ በመነሳት ነው ከ16ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ በፍጹም ሞናርኪዎች አገዛዝና በታላላቅ ፈላሳፋዎች ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና የአገር ግንባታ መካሄድ የጀመረው። ይህ በተግባር ሲተረጎም ፣ የፍጹም ሞናርኪዎች ሚና የማኑፋክቱር አብዮት እንዲካሄድ በተለይም ለነቁ ኃይሎች(active forces) አስፈላጊውን የገንዘብ ዕርዳታ መስጠት ነበር። በተለይም በማደግ ላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎችን(Infant industries)ከውጭ በሚመጡ ተመሳሳይ ምርቶች እንዳይጎዱ የዕገዳ ፓሊሲ ማካሄድ ነበር። ወደ ውስጥ ለሰፊ ገበያ ማነቆ የሆኑ የኬላ ዕገዳዎችን በማንሳት የሀብት እንቅስቃሴ እንዲካሄድ ሁኔታውን

ማመቻቸት ነበር። በዚህ ዐይነቱ የጣልቃ ገብነት ፖሊሲ ምቀኝነትና ተንኮል ቦታ አልነበራቸውም። አብዛኛዎቹ የተማሩና በፈላስፋዎች የሚመሩ ስለነበር እንዴት አድርገን የጠነከረ አገርና ህብረተሰብ እንገነባለን ነበር ህልማቸውና ተግባራቸው። እንደዛሬው እንደኛ የኢህአዴግ የምቀኛ አገዛዝ በሁሉም ነገር ውስጥ ጣልቃ በመግባትና ለማደግ ደፋ ደፋ የሚለውን ጭንቅላት ጭንቅላቱን በመምታት ህሞቱ እንዲፈስ የሚያደርጉ አለነበሩም። ይህንን ዐይነቱን በመንግስት የተደገፈ የኢኮኖሚ ፖሊስ አሜሪካን በእነ አብራሃም ሊንከንና በእነ ሃሚልተን ዘመን ፣ ጀርመን ደግሞ በንጉስ ፍሪድሪሽ ሁለተኛውና በኋላ ደግሞ በቢስማርክ አማካይነት ተግባራዊ በማድረግ ለጀርመን በአጭር ጊዜ ውስጥ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚመራ የኢንዱስትሪ አብዮት ያካሄዱበትን ሁለ-ገብ ስትራቴጂ ማየት እንችላለን። በዚህ ዐይነት በዕውቅ ላይ በተመሰረተ በመንግስት የተደገፈ ፖሊሲ ጀርመን ሁለት ትውልድ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ እንግሊዝንና ፈረንሳይን ቀድማ መሄድ ችላለች።

ወደ ጃፓን ስንመጣ ደግሞ በሜጂ ዲይናስቲ ተግባራዊ የሆነው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ከኋላ የመያዝና "catch-up" የመቅደም ስትራቴጂ ነው። ካርል ሞስክ የተባለው የጃፓን ኤክስፐርትና ፣ እንዲሁም ደግሞ ፕሮፌሰር ሊያን ግሪንፊልድ ዘ ስፒሪት ኦፍ ካፒታሊዝም በሚለው ግሩም መጽሀፋቸው ውስጥ ስለ ጃፓን የኢኮኖሚ ዕድገት ሲያትቱ መሰረቱ የተጣለው ከ1600-1868 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በቶኩጋዋ ዲይናስቲ ዘመን እንደሆነ ያስረዳሉ። በዚያን ጊዜ የነበሩ የፊዩዳል ባላባቶች በመሀከላቸው ስምምነት በመፍጠር በገጠር ውስጥ የእርሻ ምርት እንዲያድግና ከተማዎች እንዲያብቡ በማድረግ Prot-Industrial Economy እንዳካሄድና ፣ ይህ የጎጆ ኢንዱስትሪና የከተማዎች ግንባታ ለሰዎች ተሰባስቦ መኖር አመቺ ሁኔታ ሲፈጥር ፣ በኋላ ብቅ ላለው የሜጂ ዲይናስቲ መነሻ እንደሆነላትና በመንግስት የሚደገፍ ሰፋ ያለ አገር አቀፍ የኢንዱስትሪ ግንባታ ማካሄድ እንደ ጀመረ ያስረዳሉ። የሜጂ ዲይናስቲ ዋና ፍልስፍና ሀብት መፍጠርና አገር መገንባት ሲሆን ፣ በሚሊታሪ ደግሞ ጠንክሮ መገኘትና ፣ ይህንን ግብ ለመምታት ሰፋ ያለ የኢንፍራስትራክቸር ግንባታ ማካሄድ ነበር። ይህ ሁኔታ ለኢንዱስትሪ አብዮት አመቺ መንገድ ይከፍትለታል። በመቀጠልም ዘመናዊ የሆነ የናቫልና የወታደር ተቋም ይገነባል። በዚህም መሰረት ራሱን በማጠናከር ከምዕራቡ ዓለም የሚመጣበትን ግፊት ለመቋቋም ሁሉን ነገር ያመቻቻል።

ወደ ተጨባጩ የግንባታ ፖሊሲ ስንመጣ ዋና መቀመጫውን ቶኪዮ ያደረገው የሜጂ ዲይናስቲ ሰፊው ህዝብ እንዲማር የግዴታ የመሰረተ ትምህርት እርምጃ ይውሰዳል። በተጨማሪም ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ ዕድገት የሚያመች ልዩ ዐይነት የኢንጂነሪንግ ፋክሊቲ በመክፈት አዲስ ኤሊት እንዲኮተኮት ያደርጋል። የገንዘብ ምኒስተሩ ደግሞ በ1882 ዓ.ም ባንክ ኦፍ ጃፓን የሚባለውን በማቋቋም ለግል ባንኮች መመሰረት መሰርቱን ይጥላል። በዚህ አማካይነት ለኢንዱስትሪ ዕድገትና መስፋፋት ሰፊ የፊናንስ ሲይስተም ይገነባል። በተለያዩ ደሴቶች ከተማዎች መሀከል ግኑኝነት እንዲፈጠር በእንፋሎት ሃይል የሚነዳ የባቡር ሃዲድ እንዲስፋፋ ሁሉን ነገር ያዘጋጃል። በዚህ መሰረት የጃፓን ህዝብ እንደ አንድ ህዝብ ሆኖ እንዲነሳ መሰረቱን ጣለ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኢኮኖሚ ዕድገት ፍጥነት እንዲኖረውና የኢንዱስትሪዎች የማምረት ኃይል ከፍ እንዲል አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከውጭ በማስመጣትና በመኮረጅ የኢንዱስትሪዎች ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል። ባጭሩ ለጃፓን ዕድገት የመንግስት ጣልቃ ገብነት ብቻ ሳይሆን ዋና መሰረቱ ፣ ዕውቅናን ያዘለ ስልትን በመከተልና በከፈተኛ ዲሲፕሊን በመመራት ስኬታማ አደረጃጀትን በማዘጋጀት የኢንስቲቱሽኖችና የህዝቡ እንዲሁም የኤሊቱ መመሪያ በማድረግ ነው። ዲሲፕሊን በሌለብት ፣ የስራ ባህልና ፍላጎት ባልዳበረበት ፣ በዚህ ላይ ደግሞ ብሄራዊ ስሜት ባልታከለበት አገር ውስጥ አንድ አገር ሁለ-ገብ የሆነን የኢኮኖሚና የህብረተሰብን ዕድገት ልትቀዳጅ እንደማትችል ከሆላንድ እስከጀርመንና እስከ ጃፓና ድረስ ያለው የዕድገት ፈለግ ያረጋግጥልናል። ይህንን መሰረተ-ሃሳብ ፕሮፌሰር ሊያህ ግሬንፊልድ በመጽሃፋቸው ውስጥ ያሰምሩበታል። በሳቸውም ዕምነት በግለሰብኝነት ላይ የተመሰረተ ነፃነትና የብሄራዊ ስሜት(Nationalism) ወይም Individualistic –civic type of nationalism በመኖር ብቻ ነው በብዙ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ካፒታሊዝም ሊያድግ የቻለው። ለዚህ ደግሞ የመንግስት

ሚና ከፍተኛ ቦታን ሲይዝ ፣ አደናቃፊና ምቀኛ ሳይሆን አጋዥና አመቺ ሁኔታዎችን ፈጣሪ መሆን እንዳለበት በግሩም ብዕራቸው በዝርዝር ያስረዱናል።

በዚህ መልክ በጃፓን ብቻ ሳይሆን ካፒታሊዝም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ደርሶም ቢሆን የመንግስት ሚና በሌላ መልክ ቀጠለ እንጂ ሙሉ በሙሉ ከእንግዲህ ወዲያ ሁሉንም ነገር ለገበያው ኃይሎች ብሎ ጓዙን ጠቅልሎ የወጣበት ቦታ የለም። በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የብዙ የምዕራብ አውሮፓ አገር ኢኮኖሚዎች በመከስከሱ ከጦርነቱ አገግመው የወጡት እንደፈረንሳይና ጀርመን የመሳሰሉት አገሮች በመንግስት ጣልቃ-ገብነት አማካይነት ከተማዎቻቸውን እንደገና መገንባት ፣ ኢንዱስትሪዎቻቸውን መጠጋገንና የሳይንስና የቴክኖሎጂ መሰረት ለመስጠት ዩኒቨርሲቶቻቸውንና ኮሌጆቻቸውን በአዲስ መልክ በማዋቀር አጠቃላይና ሁለ-ገብ ግንባታቸውን ነው የቀጠሉት። የኒዎ-ሊበራልዚም ርዕዮተ-ዓለም ከመቃብሩ ከወጣ በኋላ ከ1975 ዓ.ም ጀምሮ ፣ በተለይም ከ1980ዎቹ ዐመታት ጀምሮ የመንግስት ጣልቃ-ገብነት እንደሰይጣን ስራ በመወሰድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለንጹህ የገበያ ፖሊሲ በስተቀር መፍትሄ የለም በማለት ብዙ የሶስተኛውን ዓለም አካዳሚሺያኖች ማሳሳት ጀመረ። ብዙ የዋሆች ወደ ተግባር ሲለወጥ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የማይችለውን የኒዎ-ክላሲካል የኢኮኖሚ ቲዎሪን የሙጥኝ ብለው በመያዝ በቀጥታ ለአገሮቻቸው ውድቀት ሁኔታዎችን አመቻቹ። ሀብት እንዲባክን ፣ ሰው እንዲበታተን ወይም አገሩን ጥሎ እንዲወጣና በሰው አገር ተንከራቶ እንዲኖር አደረጉ። ምክንያቱም ቀላል ነው። በአገር ውስጥ ዕድገት ሲኖር ፣ እያንዳንዱ ግለሰብ ተምሮና የስራ ዕድል አግኝቶ ቤተሰብ መስርቶና ልጆች ወልዶ የኑሮን ጸጋ የሚጎናፀፍ ከሆነ ከአገሩ የሚሰደድበት ምክንያት የለም። ከ1950ዎቹ ጀምሮ በኒዎ-ክላሲካል ወይም በኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚክስ ትምህርት የተኮተኮተው ቢሮክራሲና የቴክኖክራት ኃይል ፣ አገር ፣ ህብረተሰብ ፣ ብሄራዊ-ነፃነት ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ኢኮኖሚ ፣ መንፈስን የሚያድስና ጥንካሬ የሚሰጥ ፣ እንዲሁም እሴትን የሚያጎናጽፍ ባህል መገንባትን እንደመመሪያው አድርጎ ባለመውሰዱ ወይም ደግሞ ባለማወቁ እንደ ኢትዮጵያ የመሳሰሉትን አገሮች በአሜሪካ ጉያ ስር ተወሽቀው እንዲታሹ በማድረግ የመጨረሻ መጨረሻ ውድቀት ላይ ጣላቸው። ጃፓንና ደቡብ ኮርያ ዛሬ ደግሞ ቻይና እንደሚያረጋግጡልን ራሱን ለውጭ ኃይል ያላጋለጠ ፣ ብሄራዊ  አጀንዳን ያስቀደመ ፣ እንዲሁም ደግሞ በዲሲፕሊናን በታታሪነት የሚሰራ ኤሊት የመጨረሻ መጨረሻ ተልዕኮው ዕድገትን ማምጣትና ህዝቡ ተከብሮ እንዲኖር ማድረግ ነው። የእነ አቶ መለስ አገዛዝ ችግርም ይህንን  በሰፊው አለማጥናትና ከሰውነት ጋር አለማዋሃድ ነው። ተንኮልንና ምቀኝነትን በማስቀደም ዕድገት የሚባል ነገር ተግባራዊ የሚሆን እየመሰላቸው በሰማንያ ሚሊዮን ህዝብና በመጭው ትውልድ ላይ ያፌዛሉ ፤ የታሪክ ወንጀል ይሰራሉ። የእነ አቶ መለስ የዴቬሎፕሜንታል የመንግስት ፖሊሲ ብሄራዊ ባህርይ የሌለው ፣ አገርና ህብረተሰብ የሚሉትን መሰረተ-ሃሳቦች ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ዘለዓለማዊ ድህነትን የሚያጎናጽፍ አደገኛ ፖሊሲ ነው። አጀንዳቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን የጥቂቶችና ለጥቂቶች ተብሎ የተዘጋጀ ነው። ከዚህ ስንነሳ በእርግጥ እነ አቶ መለስ እንደሚሉን በመንግስት የሚደገፍ የታቀደና ሁለ-ገብ የኢኮኖሚ ፓሊሲ እያካሄዱ ነው ወይ? ከ21 ዐመት የኢህአዴግ አገዛዝ በኋላ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እየተሳሰረ የመጣና በብዙ ሚሊዮን ለሚቆጠረው በሰራ ጥማት ለሚሰቃየው ህዝባችን የስራ ዕድል እየሰጠው ነው ወይ? ሰፋ ያለ የውስጥ ገበያስ ዳብሯል ወይ? ኢህአዴግ 21 ዐመት ያህል ተግባራዊ ሲያደርግ የቆየው የኢኮኖሚ ፖሊሲስ በእርግጥስ ወደ ርስበርሱ የተሳሰረ ኢኮኖሚ ግንባታ የሚያመራ ነው ወይ ? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ኢህአዴግ 21 ዐመት ያህል ሲመራበት የከረመውን ፖሊስ ጠጋ ብለን እንመርምር።

# በእርግጥስ የኢህአዴግ አገዛዝ ልማታዊ መንግስት

# ነው ወይ ?

ኢህአዴግ ስልጣን ከጨበጠ ከሁለት ዐመት በኋላ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ጋር በመስማማት ድርጅቱ ያቀረበለትን የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች አንድ በአንድ ተግባራዊ ያደርጋል። የፖሊሲውን ምንነትና በተግባር ላይ ሲመነዘር ምን ዐይነት ውጤት እንደሚያመጣና እንዳመጣ ከዚህ ቀደም ባወጣኋቸው ጽሁፎቼ ላይ በሰፊው አብራርቼአለሁ። ጽሁፎቼን እንደገና ማገላበጡ የኢህአዴግ አገዛዝ የልማት መንግስት መሆኑና አለመሆኑን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል ብዬ አምናለሁ

ያም ሆነ ይህ እ.አ በ1993 ዓ.ም ተግባራዊ የሆነው የተቅዋም ፖሊሲ(Structural Adjustment Program) ቲዎሪያዊ መሰረቱ ኒዎ-ሊበራሊዝም ነው። ይህም ማለት ቲዎሪው በይዘት ላይ ያተኮረ ሳይሆን ክስተታዊ ነው ማለት ነው። በሌላ አነጋገር በቲዎሪው መሰረት የአንድን አገር ወይም ህብረተሰብ ኢኮኖሚም ሆነ አጠቀላይ ህብረተሰብአዊ ችግር የሚረዳው ወደ ውስጥ በመግባትና በሰፊውና በጥልቀት በማጥናት ችግሩን በማወቅ ሳይሆን የተወሰኑ የማክሮ ኢኮኖሚ መሳሪያዎችን በመውሰድና ከዚህ በመነሳት ችግሩ እንደሚፈታ ለማሳመን በመሞከር ነው። ሀለተኛ ፣ የእነ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የማክሮ ኢኮኖሚ ሞዴል የአንድን ህብረተሰብ ችግር ከኢኮኖሚ አንፃር ብቻ ነው የሚመለከተው። ከመጀመሪያውኑ ፖለቲካዊ ፣ ኢንስቱቲሽናዊ ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ነገሮችን በማጣመር የችግሩን ጥልቀት ለመረዳት ጥረት አያደርግም። ለምሳሌ የካፒታሊስትን ስርዓት የዕድገት ታሪክ ስንመረመር ከባህል አብዮት በፊት ከመጀመሪያውኑ በተወሰኑ መሳሪያዎች ብቻ የነበሩባቸውን የኢኮኖሚ ችግሮች ለመፍታት አልቃጡም። በሶስተኛ ደረጃ ፣ ከዚህ በፊት ደጋግሜ ለማብራራት እንደሞከርኩት የማክሮ ኢኮኖሚ ሞዴሉ አጠቃላይ የሆነ ህብረተሰብአዊ ሀብትን ለመገንባት የሚያስችል አይደለም። ሞዴሉ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ የሀብት ሽግሽግ በማድረግ የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል። በዚህ መልክ ፊጣሪና ኢንቬስት ለማድረግ የሚችል አዲስ ኃይል ብቅ እንዳይልና እንዳያድግ ያደርጋል። በአራተኛ ደረጃ ፣ በማኑፋክቱር ላይ ከተመሰረተ የምርት እንቅስቃሴ ይልቅ ንግድና የተቀረው የአገልግሎት መስክ እንዲስፋፋ ያደርጋል። በተለይም ከአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገትና ፍላጎት እንዲሁም የሀብት አቅርቦት ጋር ሊሄዱ የማይችሉ ትላልቅ ሆቴል ቤቶች በመስራት ውሃንና ኃይልን እንዲሁም ምግብን በከፍተኛ ደረጃ እንዲጋሩ የሚያደርግ ነው። በዚህ መልክ ያልተስተካከለ ዕድገት እንዲኖር ማገዙ ብቻ ሳይሆን የአብዛኛው ህዝብ አትኩሮ በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲሆን ያስገድዳል። በአምስተኛ ደረጃ ፣ ሰፋ ያለ የስራ ክፍፍል እንዳይዳብር ዕንቅፋት ይሆናል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አገዛዙ በሚከተለው የተቀናቃኝ ፖሊሲ በግል ሀብታቸው የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን ቀስ ቀስ እያለ ያጠፋቸዋል። ምክንያቱም በኢኮኖሚ እያደገና እየዳበረ የሚመጣ ኃይልም ለፖለቲካ አገዛዝ አያመችም በማለት አይ በሙስና ውስጥ እንዲዘፍቅ ያደርገዋል ፣ ካሊያም ደግሞ ሀበቱን በመንጠቅ ያዳክመዋል። ስለሆነም እንዲዚህ ዐይነቱ የኢኮኖሚ ሞዴል ተግባራዊ በሆነባቸው አገሮች በሙሉ ሰፊ ውንብድና መስፋፋቱ ብቻ ሳይሆን የመንግስት መኪናዎች የበለጠ ጨቋኝ እየሆኑ በመምጣት ህዝቦች አፎይ ብለው እንዳይኖሩ ተደንግጎባቸውል። ተፈጥሮአዊ መብታቸው በመነጠቅ በፍርሃት ዓለም ተውጠው እንዲኖሩ የተገደዱ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች በየአገሩ እንዳሉ የታወቀ ነው። በስድስተኛ ደረጃ ፣ ለአንድ አገር ዕድገት አስፈላጊው የሆነው የሳይንስና የቴክኖሎጂ ምርምርና ምጥቀት እንዳይኖር ከመጀመሪያውኑ ያግዳል። ሳይንስና ቴክኖሎጂ ካልዳበሩ ደግሞ የተለያዩ የምርት ማምረቻ መሳሪያዎችንና ፣ እንዲሁም ለአንድ ህብረተሰብ አስፈላጊ የሆኑ የፍጆታ ዕቃዎችንንም ሆነ ከአደጋ ሊከላከሉ የሚችሉትን መሳሪያዎች ሊያመርት አይችልም ማለት ነው። በአንጻሩ ግን ዕውነተኛ በመንግስት የተደገፈ የልማት ፖሊሲ ያካሄዱ አገሮች በሙሉ ቅድሚያ የሰጡትና አሁንም የሚሰጡት በቴክኖሎጂ ላይ

የተደገፈ ኢኮኖሚ መገንባትን ነው። ዋና ዓላማቸውም ሰፋ ያለና የጠለቀ ሀብት በመፍጠር ጠንካራ አገር መመስረት ነው። ለዚህም ነው ዛሬ ራሳቸውን መቻልና መከበር የበቁት።

ከዚህ ስንነሳ ኢህአዴግ ስልጣን ከጨበጠ ጀምሮ የሚያካሄደው የኢኮኖሚ ፖሊሲ በምንም መልኩ ሰፋ ያለ ሀብት የሚፈጥር አይደለም። የቢራ ፋብሪካ ማስፋፋት ፣ በሰሊጥ ተከላ ላይ በማትኮር ጥሬ ሀብቱ አገር ውስጥ እስከመጨረሻ ድረስ እንዳይመረት አድርጓል። በዚህም መልክ መሰረታዊ የሆነን የኢኮኖሚ ህግን ጥሷል ፤ እየጣሰም ነው። አንድ አገር የጥሬ ሀብቷን እንዳለ ከነነፍሱ ወደ ውጭ የምትልክ ከሆነ በኢኮኖሚ ልታድግ አትችልም። በአስራ አምስተኛውና በአስራስድሰተኛው ክፍለ-ዘመን ይህንን የተገነዘቡት እንግሊዝና ፈረንሳይ በጊዜው የነበረባቸውን የኢኮኖሚ ድክመት ለመቅረፍ የወሰዱት እርምጃ የግዴታ የጥሬ-ሀብት ወደ ውጭ እንዳይላክ በማድረግ ነበር። በአስራአራተኛውና በአስራአምስተኛው ክፍለ-ዘመን ጣሊያን በኢኮኖሚ የበለጸገች ስለነበረች እንደ እንግሊዝ የመሳሰሉትን የጥሬ-ሀብት አምራች አድርጋ ነበር። በጊዜው ስልጣን ላይ የነበረው በሄነሪ ሰባተኛው የሚመራው አገዛዝ ይህንን በመረዳት ወደ ማኑፋክቱር አብዮት በመሸጋገር የበግ ሱፍና ሌሎች የጥሬ-ሀብቶች ወደ ውጭ እንዳይወጡ ነው ያገደው። እንደዚሁም ፈረንሳይ በእነ ኮልበርት ዘመን ከእንግሊዝ የሚመጣባትን የኢኮኖሚ ጭነትና መዛባት ለመቋቋም የቻለችውና ወደ ኢንዱስትሪ አብዮት ለመሸጋገር የበቃችው የጥሬ-ሀብቷን በመቆጣጠርና እዚያው አገር ውስጥ ደረጃ በደረጃ እንዲመረት በማድረግ ነው። ከዚህ ስንነሳ የኢህአዴግ ፖሊሲ አንድ በአንድ የዴቬሎፐሜንታል ስቴትን የኢኮኖሚ ፖሊሲን የሚጻረርና አገራችንን ለረዥም ዐመታት ደካማና ደሀ እንዲሁም በውጭ ኃይሎች ተጠቂ የሚያደርጋት ነው።

ሰለሆነም ከአምስት ዐመት ጀምሮ ህዝባችንን ከመሬት እያፈናቀለ ኢንቬስተሮች ለሚባሉ የሚሰጠው ሰፋፊ የጋሻ መሬት በመሰረቱ የዴቬሎፐሜንታል ስቴትን የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚቃወም ነው። 1ኛ) እንደዚህ ዐይነቱ የመሬት ማፈናቀል እርምጃ የተወሳሰበና እርስ በርሱ የተያያዘ በቤተሰብ ላይም ሆነ በአነሰተኛና በማዕከለኛ ገበሬዎች የሚታረስ የእርሻ ክንውን እንዳይካሄድ ያግዳል። 2ኛ) ለኢንቬስተሮች የተሰጠው የእርሻ መሬት ለአገር ውስጥ ፋብሪካዎች የጥሬ-ሀብት እንዳያመርት ታግዷል። 3ኛ) አንድ ወጥ የሆነ የአመራረት ስልትና በተወሰኑ ምርቶች ላይ ያተኮረ የእርሻ ክንዋኔ እንዲካሄድ ይገፋፋል። ይህ ደግሞ የተፈጥሮን ህግ የሚጻረርና የአካባቢን መዛባትን የሚያስከትል ነው። ከዚህም ባሻገር በላቦራቶሪው ውስጥ የተዳቀሉ ዘሮች ከመሬት ውስጥ ውሃን የመምጠጥ ኃይላቸው ከፍ ያለ ስለሆነ ከረዥም ጊዜ አንጻር ድርቀትን ያስከትላሉ። 4ኛ) በገጠር ውስጥ የስራ-ክፍፍል እንዳይዳብር ከማገዱም ባሻገር ገበሬው ኮሙኒቲ እንዳይመሰረት ያደርገዋል። ይህም ማለት በገጠር ውስጥ በልዩ ልዩ መልኮች የሚገለጽ የባህል እንቅስቃሴ እንዳይኖር ያግዳል። አሁን ደግሞ የስኳር ምርት ለማስፋፋት የሚያካሄደው እርምጃና ወደ ሰድስት የሚጠጉ የስኳር ፋብሪካዎች ተከላ ዕቅድ የአገራችንን ኢኮኖሚ እንዲዛባ ያደርገዋል። ልክ እንደ ብራዚል ገበሬውን ወደ ተራ ባርነት እንዲቀየር የሚያደርግ ነው። ይህም ማለት ይህ ዐይነቱ ፖሊሲ የዴቬሎፐሜንታል ስቴትን መሰረተ-ሃሳብ ይፃረራል። በተጨማሪም የአበባን ተከላ ማስፋፋትና ቡናን የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ዋና ዕምብርት ማድረግና ሊሎች አጠቃላይ የሀብት ፈጠራን የማያመጡ ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔዎች በመሰረቱ ከዴቬሎፐሜንታል ስቴት ፖሊሲ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም። ታቃራኒው ናቸው ማለት ነው።

ወደ ከተማዎች ስንመጣ ፣ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለልማት እየተባለ የሚካሄደው የመሬት ንጥቂያና ተፈናቃዮች ራሳቸውን እንዲገሉ ወይም በየሜዳው ወድቀው እንዲቀሩ ማድረግ ከዴቬሎፐሜንታል ስቴት ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም አይደለም። ዕውነተኛ በመንግስት የሚደገፍ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የህዝብን መብት የሚረግጥና ከቦታቸው የሚያፈናቅል አይደለም ፤ መሆንም የለበትም። አካባቢው መልማት ካለበት ደግሞ የግዴታ ለብዙ ዐመታት በቦታው የሚኖር ሰው ሌላ አማራጭ ማግኘት አለበት ፤ ወይም ደግሞ የቀድሞው ቦታ ሊመለሰ የሚችልበት ሁኔታ ከመጀመሪያውኑ መታቀድና መዘጋጀት አለበት። የኢህአዴግ ፖሊሲ ግን በተለይም ደሀውንና ድጋፍ የሌለውን የህበረተሰብ ክፍል የሚመታና ሶሻል ዳርዊኒዝምን የሚያስፋፋ ነው። በተለይም በሪል ስቴት ስራ የተሰማሩ ከዓለም አቀፍ

የፊናንስ ካፒታል ጋር የተቆላለፉ ኃይሎች የሚሰሩት የታሪክ ወንጀል በቀላል ቋንቋ የሚገለጽ አይደለም። ከዚህም ከዚያም በመምጣትና በመሰባሰብ ፣ እንዲሁም ከውጭ የገንዘብ አበዳሪ ኃይሎች ጋር በመመሰጣጠር የሀብት ቁጥጥር እያደረጉ ነው። ህዝባችን በአገሩ ውስጥ ሁለተኛ ዜጋ እየሆነ እንዲታይ ተደርጓል። በኮሞዲቲ ገበያም ያለው ሁኔታ ከዚህ የሚያንስ አይደለም። የተሰተካከለና ሚዛናዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚቀናቀን ኃይል በመፍጠር አገራችንን ዘለዓለሟን የጥሬ-ሀብት አምራች ሆና እንድትቀር የሚያደርግ ነው። በዚህም ምክንያት ቡና አምራቹ ገበሬ ህዝባቸን ኑሮው በምንም ዐይነት አለተሻሻለም። ከጎጆ ቤቱ አልተላቀቀም። ልጆቹን ለማስተማር አንዳይችል ሆኗል። በሚያገኘው በዓለም ገበያ ላይ በሚወሰን ዋጋ የምርቱን ሂደትና ኑሮውን ለማሻሻል የቻለ አይደለም። በአንጻሩ ግን የኮሞዲቲ ገበያውን የሚቆጣጠሩት ግለሰቦችና የመንግስት ባለስልጣናት ልዩ ዐይነት ኑሮ በመኖር ለዋጋ መናርና ለሀብት ነጠቃ ምክንያት ሆነዋል ማለት ይቻላል።

ከዚህ ስንነሳና በተለይም እየጨመረ የመጣውን ድህነትና የቆሸሸ መኖሪያዎችን አካባቢ ስንመለከትና በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣውን የኑሮ ውድነት ስንመረምር የኢህአዴግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አባዛኛውን ህዝብ የባሰውኑ ወደ ድህነት የገፈተረና ወደፊትም የሚገፈትር ነው። ይህ በውስጥና በውጭ ኃይሎች በተቀነባበረና በረቀቀ መልክ የሚካሄደው ኢኮኖሚያዊ መዛባትና ፣ እንዲሁም የሀብት ቁጥጥርና ዘረፋ ልዩ ዐይነት የህብረተሰብ ግኑኝነት እየፈጠረ ነው ማለት ይቻላል። እንደዚህ ዐይነቱን በዓለም አቀፍ ፊናንስ ካፒታል የሚደገፈውን የኢኮኖሚ ፖሊሲና የሀብት ዘረፋ ዘመናዊ ፊዩዳሊዝም ተብሎ ሊጠራ ይቻላል። በዘመናዊነትና በዕድገት ስም ገበሬውን ወደ ቀን ሰራተኛነትና ወደ ጥገኝነት የሚለውጠው ነው። ከዚህ ስንነሳ ምን መደረግ አለበት ወደሚለው እናምራ።

# ምን መደረግ አለበት !

የኢህአዴግ አገዛዝ ከመሻሻልና ራሱን ከማረም ይልቅ በተለይም ባለፉት ሰባት ዐመታት እየባሰበት የመጣ አገዛዝ ነው። በአፍሪካ ውስጥም ተወዳዳሪነት የሌለው ጨቋኝ አገዛዝ ብቻ ሳይሆን አገራችንን በሁሉም አቅጣጫ እንድትዳከምና በዘለዓለማዊ ውዝግብ ውስጥ ወድቃ ህዝቧ ነፃነትን እንዳይቀዳጅ የሚያደርግ አስቸጋሪ አገዛዝ ሆኖ ብቅ ብሏል። ራሱ አገዛዙ በህዝባችን ላይ ሽብርተኝነትን እያካሄደ እያለ ለነፃነትና ለመብት የሚታገሉ ኃይሎችን በሽበርተኝነት የሚወነጅል አገዛዝ ነው። የአንድ አገር ህልውና ስልጣን ላይ ባለው የገዢ መደብ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በጠቅላላው ህዝብም የመንፈስ ጥንካሬና በስነስርዓት መኖር ነው። ለዚህ ደግሞ ኢኮኖሚ ቁልፍ ቦታን የሚይዝና ፣ የአንድ አገር ውድቀትና ጥንካሬ በኢኮኖሚ ሁኔታ የሚወሰን ነው። አንድ አገዛዝ ሆን ብሎ አንድን አገር የሚያዳክም ከሆነ ፣ ከውጭ ኃይሎች ጋር በመመሰጣጠር ሀብቷ እንዲዘረፍ የሚያደርግ ከሆነ ፣ ባጭሩ ህልውናዋን የሚያዳክም ከሆነ በህዝብ ዘንድ ምንም ዐይነት ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። የአንድ አገዛዝ ዕውቅናና ተቀባይነት ሊወሰን የሚችለው በሚሰራው ጥሩም ሆነ መጥፎ ተግባር ነው። እንዲያው በህገ-መንግስት ብቻ እያታለለ ሊኖር ምንም መብት የለውም ማለት ነው።

ከዚህ ስንነሳ የአንድ አገር ዕድገትና ህልውና ሊወሰን የሚችለው ባለው የፖለቲካና የመንግስታዊ አወቃቀር ሁኔታ ነው። ይህም ማለት አንድ አገዛዝ ራሱንና የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ለማደለብ ሲል የመንግስቱን መኪና የባሰ ጨቋኝ የሚያደርግ ከሆነና ከውጭ ኃይሎች ጋር በብዙ ድሮች የተሳሰረ ከሆነ ለአገር ህልውናና ለጠቅላላው ህብረተሰብ ተስማምቶ መኖር አደገኛ ነው። አንድ ህዝብ እየተዘረፈ ፣ እየተጨቆነ ፣ የኑሮው ሁኔታ እየተበላሸበትና አቅጣጫውም የሚጠፋው ከሆነ ይህ እንደተፈጥሮ ህግ መታየት የለበትም። የሰው ልጅ ከእንስሳ የሚለየውም እንደዚህ ዐይነት ነገር እንዴት ሊመጣ ቻለ ብሎ በመጠየቅ ራሱንና አካባቢውን ለመለወጥ የሚችል ከሆነ ብቻ ነው። ሁኔታውን ለመለወጥም ሆነ ለማሻሻል የማይችል ምሁርም ሆነ ህዝብ በታሪክ

ውስጥ እየተጠቃ የሚኖርና በመጭውም ትውልድ ተጠያቂ የሚያደርገው ነው። ስለዚህ ለአንድ አገር ዕድገት ቁልፉ የመንግስቱ አወቃቀር ሁኔታና የሚያካሄደው የፖለቲካ ዐይነት ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ። በታሪክም እንደተረጋገጠው የፖለቲካ ሁኔታ ሲሻሻልና ህዝቡም ነጻነትን ሲቀዳጅ ነው ሃሳብ ሊመጣለትና ህብረተሰቡንም ሆነ ኢኮኖሚውን ሊያሳድግ የሚችለው። በሌላ አነጋገር አንድ ህዝብ የበለጠ ነጻ እየሆነ በመጣ ቁጥርና ከላዩ ላይ ያለው ጭነት ሲቃለልለት የመፍጠር ኃይሉም ይዳብራል ፤ ህብረተሰብአዊ ሀብት ይፈጥራል። ስለዚህም የፖለቲካ ጥያቄና የመንግስቱ መኪና ጉዳይ ቁልፍ ቦታን ይይዛሉ ማለት ነው። ህዝባዊ ባህርይ እንዲይዙና ታሪካዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ በአዲስ መልክ መደራጀት አአለባቸው። ህዝብን ከማስፈራራት ይልቅ የህዝብ ወዳጅና አለኝታ መሆን አለባቸው። ህብረተሰብአዊ ፍቅርን የሚለግሱና አገራችን ተከብራ እንትኖር የሚያድርጉ ሆነው መደራጀት አለባቸው። የሰላዮች መጨፈሪያ መሆን የለባቸውም። ባጭር ቋንቋ የኢህአዴግ ታሪካዊ ተልዕኮው ጥፋት በመሆኑና ሊታረምም የማይችል ስለሆነ ከኮመን ሴንስ አንፃርም ሆነ ከተፈጥሮ ህግ ሁኔታ ስልጣን ላይ መቆየት ያለበት አይደለም። ወደፊትም እንደዚህ ዐይነቱ አገር አጥፊ ኃይል የፖለቲካ ህይወት አይኖረውም ፤ሊኖረውም አይገባም።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በታሪክ ውስጥ እንደተረጋገጠው ካለኢንስቲቱሽናል ሪፎርም ምንም ነገር መስራት አይቻልም። የተቀላጠፈና ሰውን የሚያከብር አሰራር ካለ ለፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ያመቻል። ብዙ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡትና ፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴም በሰዎች የሚካሄድና በጊዜና በአካባቢ የሚወሰን እንደመሆኑ መጠን የኢንስቲቱሽን ለውጥና ፣ ኢንስቲቱሽኖች በልዩ ልዩ የስራ መስክ መዳበር ያለባችው እንደሆኑ የበለጸጉ አገሮች ታሪክ ያስተምረናል። ከዚህ ጋር ተያይዘው በመንግስት የሚደገፉ የምርምርና የጥናት እንዲሁም የቴክኖሎጂ አፍላቂ ኢንስቲቱሽኖች መቋቋም አለባቸው። ይህ ሁኔታ የግዴታ ያለውን የትምህርት ተቀዋም በአዲስ መልክ ማደራጀት እንዳለብን ይጠቁመናል። በአሁኑ ወቅት ካለበቂ ጥናትና የሰውና የማቴሪያል ኃይል ፣ እንዲሁም ካለበቂ ላቦራቶሪና ቤተ-መጻህፍት የተቋቋሙት ኮሌጆች ወይም ዩኒቨርሲቲዎች ወደ ዕደ-ጥበብ ማሰልጠኛነት መቀየር አለባቸው። ከዚህም ስንነሳ ሰፊና አጠቃላይ የሆኑ የዕደ-ጥበብ ሙያ መስኮችንና የኢንጂነሪንግ ኮሌጆችን ማስፋፋቱና ማዳበሩ ለዕድገት አመቺ ነው። የጊዜውም ጥያቄ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ መገንባት ነው። ከዚህ ውጭ ከውጭ የሚመጣን ውድድር መቋቋም አይቻልም። እንዲያውም ለዕድገት ዋናው ቁልፉ የጥሬ-ሀብት ተትረፍርፎ መገኘት ሳይሆን የዕውነተኛ ዕውቀት ባለቤት መሆን ነው። በየአገሩ እንድምናየው የጥሬ-ሀብት አገር አምራቾች በዕድገታቸው የተዛነፉና በሙስና ላይ የተመሰረተ አገዛዝ ነው ያላቸው። ይህ ዐይነቱ ሁኔታ ግን የተፈጥሮ ህግ አይደለም። ከባህል ተሃድሶ አለመኖር ጋርና ከህብረተሰበአዊ ኃላፊነት አለመሰማት ጋር የተያያዘ የአገዛዝ ስልት ሲሆን ፣ በተጨማሪም የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ከመከተል ጋር የሚያያዝ ነው።

ለአንድ አገር ዕድገት መንግስት የሚከተለው ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን ወሳኙ ፣ በአገር ውስጥ ከብዙ ክርክር በኋላ የሚዳብር የኢኮኖሚ ቲዎሪና ፖሊሲም መኖር ወሳኝ ሚናን ይጫወታል። አንድ አገዛዝም በእርግጥም ለአገሩ ዕድገት የሚቆረቆርና በታታሪነት ሊሰራ የሚችለው በጥሩ ቲዎሪና ፖሊሲ የሚመራ እንደሆነ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ በየጊዜው መመርመር አለበት። ስለዚህም አንድ አገዛዝ የሚመራበት የኢኮኖሚ ፖሊሲ የአገሩን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆን አለበት። ለውጭ ኃይሎች መፈናፈኛ የማይሰጥ መሆን አለበት። ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን ከደሙ ጋር ያዋሃደ ኢትዮጵያዊ ኃይል ያስፈልጋል። ይህ ኃይል ዕውቀት ያለው ፣ በአዋቂዎች የተከበበና ምክር የሚሰማ መሆን አለበት። ከዚህ ጋር ተያይዞ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ለአንድ አላማ በአንድነት መነሳት አለባቸው። በሳይንስ የማይረጋገጥን ርዕዮተ-ዓለም ሽፋን የሚያደርግና ከአገር ጥቅም ይልቅ ለራሱና ለውጭ ኃይሎች ጥቅም የሚታገል የፖለቲካ ድርጅት ለዕድገትና ለህብረተሰብአዊ መተሳሰር እንቅፋት እንደሚሆን ከመጀመሪያውኑ መታወቅ አለበት። ስለሆነም ለአገር እታገላለሁ ብሎ የሚነሳ ማንኛውም ኃይል ከውጭ

ኃይሎች ጋር በጥቅም የተሳሰረ መሆን የለበትም። በሌላ አነጋገር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከውጭ ኃይሎች ጋር የውስጥ ለውስጥ ግኑኝነት የፈጠረና በነሱም አማካይነት ስልጣን ላይ እወጣለሁ የሚል የመጨረሻ መጨረሻ ተልዕኮው ጥፋት ይሆናል። ከብዙ የአፍሪካ አገሮች ታሪክ የምንማረው በተለይም አሜሪካንን ተገን አድረገው ስልጣን ላይ የወጡ ኃይሎች ህዝቦቻቸውን ወደ ዕውነተኛው ነፃነት ሊያመሩት አልቻሉም። ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚሄዱ የአሰራር ዘዴዎች ወይም ባህሎች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ስነ-ምግባርና ሞራል፣ ዲሲፕሊንና የጠበቀ አደረጃጀት ግን ደግሞ በየጊዜው የሚሻሻል፣ ታታሪነትና ህብረተሰብአዊ ኃላፊነት፣ ጥበብን የሚያስቀድም የአሰራር ስልት ለአገር ዕድገት በጣም ያመቻሉ። ይህም ማለት ለፖለቲካ ስልጣን ወይም ኃላፊነት እታገላለሁ የሚል የግዴታ በራሱ ላይ የባህል ለውጥ ለማካሄድ የሚዘጋጅና ሂስንም የሚቀበል መሆን አለበት። ተነካሁ ብሎ የሚያኮርፍ ለኃላፊነት ብቃት የለውም።

ወደ ሀብት ጥያቄ ስንመጣ የኢህአዴግ አገዛዝ አዲስ የሀብት ግኑኝነትና ክፍፍል ሁኔታ ፈጥሯል። የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ሰፊውን ህዝብ ከመሬቱና ከንብረቱ አፈናቅሎታል፤ እያፈናቀለውም ነው። ይህም ማለት ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ሀብት በሙሉ ከተመረመር በኋላ በመንግስት ቁጥጥር ስር በመዋል ወደ ህዝብ የሚመለሰበት ሁኔታ ይዘጋጃል። ከዚህም በላይ በተለይም ለውጭ ኢንቬስተሮች እየተባለ የተሰጠው የእርሻ መሬት ካለምንም ካሳ ተወርሶ ለአራሹ ህዝብ ይመለስለታል። ለህዝብ መፈናቀል ምክንያት የሆኑ ባለስልጣናትና የውጭ ኢንቬስተሮች በአካባቢው ላይ ላደረሱት ጉዳትና የህዝብ መፈናቀል ተጠያቂ ሲሆኑ፣ በተለይም ኢንቬስተሮች ካሳ እንዲከፍሉ ይገደዳሉ። እዚህ ላይ በአንዳንድ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የሚናፈሰው እንደዚህ ዐይነቱ እርምጃ የዓለም አቀፍ ህግና ስምምነትን ይጥሳል የሚለው ትጥቅ አስፈቺ አነጋገር ቦታ የለውም። አገርህን አንተ በፈለግኸው መልክ አትገንባ የሚል ህግ የለም። በአንድ አገር ውስጥ የሚገኝ ሀብት ሆነ መሬትም ጭምር በዚያ አገር የሚኖር ህዝብ ሀብት ነው። እንደ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንደዚህ ካደረጋችሁ ብድር አንሰጣችሁም የሚለው ዛቻ ቦታ የለውም። ማንኛውም ከውጭ የሚመጣ ግፊትና ጫና በኛ የተባበረ ኃይልና ዕምነት ብቻ ነው ሊፈርስ የሚችለው። በመሆኑም የእርሻ መሬት በግለሰብም ሆነ በማህበር በመደራጀት ለሚያርስ ሁሉ በይዞታ ይሰጠዋል። ገበሬው መሬቱን በስነስርዓት የማልማት መብትና ግዴታ ሲኖረው፣ የመሸጥ ወይም የመለወጥ መብት አይኖረውም። ከወላጅ ወደ ልጅ የሚተላለፍ ይሆናል ማለት ነው። የከተማ ቦታዎች ደግሞ ህብረተሰቡ እንዲኖርበት ሆነው ጥበባዊ በሆነ መልክ የሚዘጋጅበት ሁኔታ ይፈጠራል። ሰፊውን ህዝብ ወደቆሻሻ መኖሪያ ቦታ የሚገፈትር አጉል ፖሊሲ ይቆማል። ሪል ስቴትስ የሚባሉ የአገርን ዕድገትና የሰፊውን ህዝብ መብት ያላከተቱና ለተወሰነው የህበረተስብ ክፍል ተብለው የሚሰሩ የህንፃ አሰራሮች እንዲቆሙ ይደረጋሉ። የሪል ስቴቶች መስፋፋት ልዩ ዐይነት ሰግሪጌሽንን የሚያመጣ ስለሆነ መቆም አለበት። ስለሆነም የከተማን ቦታ ሰፊው ህዝብ በግለሰብም ሆነ በማህበር በመደራጀት ከአራት ፎቅ በላይ ከፍ የማይል ቤት እንዲሰራ ማንኛውም ድጋፍ ከመንግስት እንዲሰጠው ይደረጋል። ለዚህ ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ ያለው፣ የተለያየ የዲንጋይ ዐይነት፣ ለጡብ የሚሆን አፈርና ሌሎች ማቴሪያሎች ለቤት ስራ የሚያመቹ ናቸው። በአውሮፓ ውስጥ የቤት አሰራርን ታሪክ ላጠና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊውን ህዝብ በማንቀሳቀስ ነው ከተማዎችንና አዳራሾችን እንዲሁም የመንግስት መስሪያ ቤቶችን መገንባት የተቻለው። ፍላጎትና ዲሲፕሊን ካለ የማይሰራ ነገር የለም ማለት ነው። ለከተማዎች ግንባታ የሚሆን አርኪቴክተሮችን፣ የህንፃ ስራ አዋቂዎችን፣ የከተማ ዕቅድ አውጪዎችን፣ ሶስዮሎጂስቶችንና ፈላስፋዎችን ያቀፈ ልዩ ኢንስቲቱት እንዲቋቋም ይደረጋል። ከውጭ ከጣሊያን፣ ከፖላንድ፣ ከፖርቱጋልና እነዚህን ከመሳሰሉት አገሮች አዋቂዎችና አናጢዎች በማምጣት ብዙ ትምህርትና ልምድ መቅሰም ይቻላል።

አንድን ከተማም ሆነ አገር ለመገንባት የገንዘብ ጉዳይ ወሳኝ ነው። ስለሆነም በሶስት አቅጣጫ የሚሰራ የባንክ አደረጃጀት መቋቋም አለበት። በየክፍለ ሀገሩ ርካሽ ብድር የሚስጡ የመንግስት ባንኮች መቋቋም አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪ ለዕድገት

*የሚሆንና በግለሰቦች እጅ ያለን ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ ልዩ የዕድገትና የመልሶ መገንባት ባንክ ይቋቋማል። ከዚህም በላይ በሳንቲም የሚቆጠር ልዩ ዐይነት ፈንድ ሪይዚንግ ሲይስተም ይፈጠራል። በዚህ መልክ የሚገኘው ገንዘብ ለየክፍለ ሀገሮች እንደፍላጎታቸውና ዕድገታቸው የመገንቢያ ዕርዳታ ይሰጣቸዋል። በሁለተኛ ደረጃ ፣ በግለሰብ ደረጃ የሚንቀሳቀስ የባንክ ኢንስቲቱት ይመሰረታል። የግለሰብ ባንኮች ጥብቅ የሆነ የአሰራር ህግን እንዲከተሉ መመሪያ ይወጣል። በሶስተኛ ደረጃ ፣ በማህበር የተደራጀና የሚተዳደር ባንክ ይቋቋማል። የእነዚህ ሁሉ የገንዘብ ምንጭ የማዕከላዊ ባንክ ሲሆን ፣ በተለይም የብደርን አሰጣጥ የሚቆጣጠር ልዩ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ይቋቋማል። በዚህ መልክ በባንክ አማካይነት ሊንቀሳቀስ የሚችል ሀብት በመፍጠር ለማኑፋክቱር ተከላና የግዴታ ለጠቅላላው የአገር ግንባታ እንዲውል ይደረጋል። በብድር የሚሰጠው ገንዘብ ወለዱ ዝቀተኛ በመሆን ከብዙ ዐመታት በኋላ የሚከፈል ይሆናል። የውጭ ገንዘብን በሚመለከት የግዴታ የውጭ ምንዛሪ በመግንስት ቁጥጥር ስር ይውላል ፤ ወይንም እንደ አስፋላጊነቱ ማዕከላዊ ባንኩ ለማሽንና ለዕድገት የሚያገለግሉ ኢንዱስትሪዎችንና የጥሬ ሀብቶችን ለማስመጣት ለአስመጨዎች ያከፋፍላል። ግለሰቦች የውጭ ገንዘብ ወደ ውጭ እንዳያወጡ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። ማንኛውም የጥቁር ገበያና የአየር ባየር ንግድ እንዲሁም ደላላነት በህግ ይከለከላሉ። ከዚህ በተረፈ ለሞራል ብልሹ የሚሆኑ የመጠጥ ዐይነቶችና ፣ ቅጥ ያጣ ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የማይጓዝ የፍጆታ ዕቃ እንዳይገባ ይታገዳል ፤ ወይም በመቶ ፐርሰንት ይቀረጣል። በተጨማሪም በአገር ቤት ውስጥ የሚመረቱ ተመሳሳይ ምርቶች ከውጭ በገፍ እንዳይገቡ ገደብ ይደረግባቸዋል ፣ ወይም ከፍተኛ ቀረጥ ይጫንባቸዋል። ከዚህ በተረፈ ከውጭ የሚመጡ ሰከንድ ሃንድ ዕቃዎች በጥብቅ የሚከለከሉና እንደ መኪና የመሳሰሉት ደግሞ የተወሰነ ስታንደርድን ያሟሉ መሆን አለባቸው። የአገሪቱን የትራንስፖርቴሽን ችግር ለመፍታት ከፍተኛ ቦታዎች ባሉበት ቦታ በአየር ላይ የሚንቀሳቅስ ቀላል ባቡር ማስገባት ፣ በዚህ ዕውቀት ካለቸው እንደ ስዊዘርላንዲና አውስትሪያ ጋር ልዩ ስምምነት ማድረግ። በረባዳ ቦታዎች ደግሞ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀስ ስትሪት ካር እንዲስፋፉ ማድረግ። በዚህ መልክ የመኪናን መግባት በመቀነስ በከተማዎች ያለውንም የትራፊክ አደጋና የመንገድ ጥቦት መቋቋም ይቻላል።*

*የአንድ አገር ኢኮኖሚ ፖሊሲው የመጀመሪያው ዓለማ የአገርን ሀብትና የሰው ኃይል በማንቀሳቀስ ድህነትን ማሰወገድ ነው። በብዙ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ከሁለተኛ ዓለም ጦርነት በፊትም ሆነ በኋላ ተግባራዊ የሆነው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ኒዎ-ሊበራሊዝም ሳይሆን በዕውቅ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ ግንባታ ነው። ጀርመን ሁለት ሶስተኛው የሚሆነው ኢኮኖሚዋና ንብረቷ በጦርነቱ ምክንያት ከወደመና ከፈራረሰ በኋላ ከአስራ አምስት እስከ ሃያ ዐመት ባለው ጊዜ ውስጥ መልሳ የገነባቸው በተዓምር ሳይሆን በመደራጀት ፣ በዲሲፕሊንና በፍላጎት በመመራት ነው። እነዚህን መመሪያዎች ያለደረገ በፍጹም ጤናማና ጠንካራ አገር ሊገነባ አይችልም ማለት ነው።*

*ይህ ማለት ምን ማለት ነው። የኢትዮጵያን ዕድገትና ስልጣኔ ከዛሬው አገዛዝ ባሻገር ማየት አለብን ማለት ነው። በምርጫ ተወዳድሬ ስልጣን ይዤ አገር እገነባለሁ ማለት ለአገዛዙ በጭቆናህ ግፋበት እንደማለት ይቆጠራል። የኢትዮጵያ ህዝብና አገር ወዳዱ ኃይል ለኢህአዴግ ህገ-መንግስት የሚዋደቅ ሳይሆን በህገ-መንግስቱ መቃብር ላይ አዲስ ህገ-መንግስት በመፍጠር ወደ አገር ግንባታ የሚሸጋገርበት መሆን አለበት። ስለሆነም ከምንጊዜውም በላይ ከውዥንብር በመላቀቅና ህዝብን ከማደናበር ታግዶ ወደ ተባበረና ለዕድገት ወደሚያመች ስራ መሰማራቱ የኢህአዴግን አገዛዝ ዕድሜ ያሳጥረዋል። የኢትየጵያ ህዝብ የሚሻውና የቀን ተሌት ህልሙ ከእንደዚህ ወደ ወሮበላነት የሚጠጋ አገዛዝ መላቀቅ ብቻ ነው።*

ፈቃዱ በቀለ

fekadubekele@gmx.de

**ማሳሰቢያ፡** በተለይም ስለኢኮኖሚ ዕድገት ያለውን አወዛጋቢ ጉዳይ ለመረዳት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መጻህፍት ማየቱ ይጠቅማል።

Angresano, James, The Political Economy of Gunnar Myrdal, UK, 1997

Blaug, Mark(ed), Thorsten Veblen: Pioneers in Economics, London, 1991

Greenfeld, Liah, The Sprit of Capitalsim, England: London, 2001

Landes, David, The Wealth and Poverty of Nations, New York, 1999

Landes, David, The Unbound Prometheus: Technological Change and Industrial Development in Western Europe from 1750 to the present, New York, 2008

Reinert, Erik, How Rich Coutries Got Rich and Why Poor Countries Stay Poor, London, 2007

Reinerr, Erik, The Role of the State in Economic Growth, Journal of Economic Studies, 26.2/5, 1999, pp. 268-326